ቁጥር OFAUF-04.20/1/14
ቀን 03/04/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለአቶ ስለሽ ለማ
የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት
ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 5 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 21 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች እና 18 ገጽ የሂሳብ ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ገነነ ወርቁ
በአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የኦዲት ሥራ አስኪያጅ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::
የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር ከ1 እስከ 4 ከተገለጹት ሁኔታዎችች በስተቀር በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>

ምንም እንኳን በሰጠነው አስተያየት ላይ ለውጥ ባያስከትሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዮቱ ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መስመር በየሥራ ክፍሉ ለቁጥጥር እንዲያመች የሚጠቀሙበት የስልክ መጠን (ተመን) ያልወጣለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በ2011 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ከመደበኛ በጀት ብር 22,114,702.91 እና ከካፒታል በጀት ብር 182,165,827.95 በድምሩ ብር 204,280,530.86 ያልተሰራበት በጀት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

- በተገቢው ሁኔታ እና በተደራጀ መልኩ የቋሚ ዕቃዎች የማይመዘገቡ መሆኑን፤
- በንብረት ክፍሉ አገልግሎት የሚሰጡ እና የማይሰጡ ዕቃዎች ተቀላቅለው የተገኙ መሆኑ፤
- በLetter Of Credit የተገዛ ልብስ ማጠቢያ ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ ያስመጠለያ የተቀመጠ መሆኑ፤
- የመለዋወጫ ዕቃዎች ቢን ካርድ ተከፍቶላቸው እየተቀናነሰ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- እያንዳንዱ ሰራተኛ የወሰደውን ንብረት ተመዝግቦ ቀሪ በእጁ ላይ ለሚቀር user card ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- Old model computer ብዛታቸው 31 እንዲሁም ሲስተም ዩኒት የሌላቸው Computere ብዛታቸው 14 በባለሙያ መስራትና አለመስራታቸው ሳይረጋገጥ በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸውን፣

**ልዩ ልዩ፣**

- በኢንስቲትዩቱ የ2011 በጀት ዓመት የዝውውር ቅጾች በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ከጸደቁ ቦኃላ በኢንስቲትዩቱ መዝገብ ቤት ክብ ማህተም ከማድረግ ውጭ ፕሮቶኮሉን ጠብቆ የመዝገብ ቁጥርና ቀን ሳይሰጠው ወጪ እንደሚደረግ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**